# <u>ወናዘዚቲ ክንፈ</u> (የክንፈ መጽናኛ)

ቤቱን መኖሪያውን እየተወ ሰው
ሰደት ብቻ ሆነ ያበሻ ዕዳው።
ጠጅም እንዳያምረኝ ድሮ ጠጥቻለሁ
ጠላም እንዳያምረኝ ድሮ ጠጥቻለሁ
ዛሬ በወያኔ ጠሜን ውዬ አድራለሁ።

በሩ ተጠርቅሞ በሻቢያ ጣጣ
ችግር ነው ማወቁ ማን ገባ ማን ወጣ።
አሁን ምን ይጠቅማል አሰብን መዝጋት
ነገ ተነገወዲያ በጦር ለመክፈት።
አሁን ምን ይጠቅማል መሬት መሰንጠቅ
ክልሉን ግዛቱን ያበሻ ሆድ ሲያውቅ።
ኑሮ ካቅም በላይ ቢወደድብኝ
ወያኔ ባንድ አፋ ሲያላግጥብኝ
ሲፈልገው ደሞ ሲተኩስብኝ
ሆ ብሎ መነሳት ምነው ተሳነኝ።
ወርቁን ቀለበቱን ሰጡልኝ ለጀግና
የኔ ጣት ጠንክሮ ቃታ አልሳበምና።
የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊለማ
ይሆናል እንጂ የጦር አውድማ።

ክንፈ ሚካዔል
ሜልበርን፣ ኸታች ኸሰር
ነሀሴ ፲፰፣ ፪ሺህ ዓ/ም